በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

የካቲት 24 ቀን 2011ዓም

## እንኳን ለኢመማ 70ኛ ዓመት ምስረታ አደረሳችሁ!!
## ለትምህርት ጥራት መጠበቅ የመምህራንን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻሉ ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ የመምህራን የመብት ጥያቄ እንቅስቃሴ የተጀመረው ዘመናዊ አገልግሎት ለሕዝብ የሚሰጡ መንግሥታዊ ተቋማት ማለትም ባንክ፣ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ትራንስፖርትና ትምህርት በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ በአጼ ኃይለስላሴ ከቀጠለበት ጊዜ ጀምሮ ነው። መምህራን የካቲት 14 ቀን 1941 ዓም በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት በተለያዩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ 32 መምህራን የመምህራን ሕብረትን መሰረቱ።የሕብረቱም ሊቀመንበር አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ነበሩ። ሕብረቱን የመሰረቱት 32ቱ መምህራን በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት በኖርማል ኮሌጅ ይሰጥ የነበረውን የሁለት ዓመታት የመምህርነት ሙያ ሰልጥነው የተመረቁ ናቸው።

ሕብረቱ እስከ 1953ዓም ድረስ ያለምንም ውጣ ውረድና የምዝገባ ጥያቄ በመንግስት ሳይጠየቅ የድርጅቱን ስራ በማካናወን ቆየ። በ1953ዓም በነ ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ የተካሄደውን መፈንቅላ መንግስት ሙከራ ደግፏል በማለት መንግስት ለሕብረቱ እውቅናና ሕጋዊ ሰውነት ነፈገ። የምዝገባ ፈቃድ ጥያቄ በማንሳትም የሕብረቱን እንቅስቃሴ ማወክ ጀመረ። በዚህም የመጀመሪያው የመንግስት ጣልቃ ገብነት ተከሰተ። በመሆኑም እስከ 1957ዓም ለ16 ዓመታት ሕብረቱ የሕጋዊ ሰውነት ምዝገባና እውቅና ተነፍጎ ቆየ። በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው የዓለም የመምህራን ሙያ ድርጅቶች ኮንፌዴሬሽን በኢትዮጵያ አዲስ አበባ በአፍሪካ አደራሽ 13ኛውን የኮንፌዴሬሽን ጠቅላላ ስብሰባ በነሐሴ ወር 1957 ዓም እንዲካሄድ በመወሰኑ፣ ኮንፌዴሬሽኑ የአሜሪካ ድጋፍ የነበረው ስለሆነ ንጉሱም ለመልካም ዝናቸው በማሰብ ስብሰባው በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ፈቀዱ። ከዚያም ሕብረቱ በመንግስት እውቅናና ተቀባይነት አግኝቶ ስሙን የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ)በሚል መጋቢት 14 ቀን 1957ዓም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያገለግል ፈቃድና ሕጋዊ ሰውነት አገኘ።

ከዚያም ኢመማ ራሱን በማጠናከርና የክፍለ አገር ቅርንጫፍ ጸ/ቤቶችን በማቋቋም በአገራችን ጥራት ያለው ትምህርት ለሕዝብ ልጆች ሁሉ በዕኩልነት እንዲሰጥ፣ እንዲደረስ፣ የመምህራን መብት እንዲከበር፣የመምህራን የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻልና ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት እንዲከበር ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል ትግል አካሄዷል። በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ባጠቃላይ ለኢመማ 70ኛ ዓመት ምስረታ እንኳን አደረሳችሁ/አደረሰን።

በዚህ መግለጫ ማንሳት የምንፈልገው መምህራን በማህበራቸው አማካይነት ለትምህርት ጥራት ብዙ ትግል ማድረጋቸውን እንዲሁም ባደርጓቸው የስራ ማቆም አድማዎች፣ ሰላማዊ ሰልፎች ፣ ስብሰባዎች ሁሉ የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻልማለትም የመኖሪያ ቤት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለቤት የሚያስፈልጉ እቃዎችን ለማሟላት የሚያስችል የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ በተለያዩ ወቅቶች ጠይቀዋል።የመምህራን የመብትና ለኑሮ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ጥያቄ ምላሽ ባለመሰጠታቸው በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥር ችሏል። መሰረታዊ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሆኑት ውስጥ ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስና የጤና አገልግሎት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያስተምሩ ለአብዛኛው መምህራን ያልተሟሉ ናቸው። ለትውስታ ያህል መምህራን ትምህርት በጥራት እንዲሰጥ፣ ሰብአዊና ዴምክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በተለያዩ ወቅቶች ያካሄዱትን የተወሰኑ እንቅስቃሴዎችንና የገጠማቸው ሳንካ በአጭሩ እናቀርባለን።
በ1960ዓም የመጀመሪያውን የመምህራንን የመብት ጥያቄ በማንሳት የስራ ማቆም አድማ ያደረገው በአቶ ከበደ ደስታ ፕሬዝዳንትነት ይመራ የነበረው የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ነበር። ይህ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አካል የነበረው

የአዲስ አበባ ማሕበር ያቀረባቸውን የትምህርት ጥራትና የመብት ጥያቄዎች ንጉሱ ተቀብለው ለጥያቄዎቹ መልስ ይሰጣል ብለው ሸንግለው በተግባር ላይ የዋለው ግን በወቅቱ የጽጥታ ሹም በነበሩት በኮሎኔል በላቸው ጀማነህ አማካይነት 20 መምህራንን ከአዲስ አበባ መምህራን መርጠው የገንዘብ ድጎማ በማድረግ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ እንዳይሰጥ ለማድረግ የአዲስ እበባ መምህራንን ለመከፋፈል ሙከራ ተደረገ።ይህም በመምህራን የውስጥ ጉዳይ  ሁለተኛው የመንግስት ጠልቃ ገብነት ነበር። አዲስ እበባ መምህራን ማህበር ግን የእነዚያን ሰላይ መምህራንን የመከፋፈል እንቅስቃሴቻውን ተቋቁም ከአባልነት ሰረዛቸው፤ በ1966ዓም የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ያደረገውን የስራ ማቆም እድማ  አገር አቀፉ  ማህበር አድማው ያለኔ እውቅና የተደረገ ነው በማለት ተቃወመ።  ከአዲስ አበባ መምህራን ማህበር የተበራሩትን 20ዎቹን መምህራን የአዲስ አበባ መምህራን አባል እንዲሆኑ ወሰነ።የኋላ ኋላ ግን የአዲስ እበባ መምህራን ማህበር የወሰደው አቋም ትክክክል እንደሆነ ከኢመማ የትግል ድርሳን ማዋቅ ተችሏል።

በ1963ዓም ከሚያዝያ 13 እስከ 15 ቀናት በአዲስ አበባ የተደረገው የኢመማ ልዩ ጉባኤ የአዲስ አበባ መምህራን ማህበርን ከኢመማ አባልነት ሰረዘው።የመምህራን ትግል በአገሪቱ በሁሉም ቦታዎች ቀጥሎ ለአዲስ አበባ መምህራን በሰጡት ድጋፍ በመስከረም ወር 1966ዓም በአርባምንጭ በተደረገው የኢመማ ጠቅላላ ጉባኤ አዲስ እበባ መምህራን ማህበርን እንደገና በአባልነት ተቀብሎ ኃይሉን በማጠናከር በታህሳስ ወር 1966ዓም አዲስ አበባ በተደረገው ልዩ የኢመማ ጉባኤ ሴክተር ሪቪው የተባለውን የድሃ ልጆች ከ8ተኛ ክፍል በላይ እንዳይማሩ የሚከለክለውን የትምህርት ፖሊሲ በመቃወም፣ ለመምህራን  የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ በመጠየቅ መልስ ለመንግስት አቅርቦ ለምላሹ የጊዜ ገደብ ሰጠ። መንግስት ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ መምህራን በኢመማ መሪነትና ጥሪ በየካቲት 11 ቀን 1966ዓም በኢትዮጵያ ውስጥ በሙሉ የድሃው ልጅ ይማር፣ ድህነት ወንጀል አይደለም፣ የሴክተር ሪቪው ትምህርት ፖሊሲ  ተግባር ላይ እንዳይውል፣ ለአዲስ ተቀጣሪ መምህራን መነሻ ደመወዝ ስኬል እንዲሻሻል፣ ለነባር መምህራን ደመወዝ ጭማሪ ፣ ዕድገትና የዝውውር መብት እንዲኖር በመጠየቅ በወቅቱ የነበረውን መንግስት ከስልጣን ለማስወገድ የረዳ አገር አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፍና አንድ ወር የፈጀ የስራ ማቆም አድማ ተደረገ። የያኔው ኢመማ  ለአባላቱ ታማኝና የአባላቱ መብት ለማስከበር የቆመ ነበር። በመሆኑም የመምህራን ህብረት ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጾታ ሳይለይ አንድነቱ  ከብረት የጠነከረ ነበር።

ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ ባለመሰጠታቸው ትግሉ ቀጥሎ በጳጉሜን ወር 1967ዓም በጅማ  በተደረገው የኢመማ ጠቅላላ ጉባኤ ደርግ ያቋቋመውን የሥራዓተ ትምህርት ኮሚቴንና የትምህርት ዝግጅትን በመቃወም፤ስርዓተ ትምህርቱ በትምህርት ባለሙያዎች የመምህራንን፣የወላጆችን፣ የተማሪዎችንና የትምህርት ባለድርሻዎችን ባከተተ መልኩ እንዲቀረፅ፣ የመምህራን የደመውዝ ጭማሪና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ማለትም አበል፣ ዕድገት፣ ዝውውር ጥያቄዎች ከሌሎች እገራዊ ጥያቄዎች ጋር (ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ ዴምክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ ይከበሩ ....ወዘተ) መልስ እንዲሰጥ ለደርግ መንግስት አቀረበ። መልስ የማይሰጥ ከሆነ በሕዳር ወር 1968ዓም የስራ ማቆም አድማ እንደሚጠራ አሳወቀ።
ደርግ ግን ለጥያቄዎቹ መልስ ከመስጠት ፈንታ ከጥቅምት ወር 1968ዓም ጀምሮ የማህበሩን ጽ/ቤት ዘጋ፣በማህበሩ አመራርና አባላት ላይ የተለያዩ ስሞችን በመለጠፍ ገደለ፣ አሰረ፣ ከአገር እንዲሰደዱም አደረገ።  ለሶስተኛ ጊዜ በማህበሩ ላይ መንግስት ጣልጋ ገብነትን ፈጸመ። የማበህበሩን ፅ/ቤት ለአራት ዓመታት(ከ1968_1971ዓም) ከዘጋ በኋላ በግንቦት 20 ቀን 1983ዓም ከስልጣን እስከተወገደበት ድረስ ማሕበሩን እንደ አንድ ፖለቲካ ክንፍ አድርጎ ከመጠቀሙም በላይ ያለመምህራን ፈቃድ ከደወወዛቸው ላይ ገንዘብ እየወሰደ በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ ዘርፏል።

ወያኔ/ኢህአዴግ በጉልበት ስልጣን ላይ  እንደወጣና የሽግግር መንግስት እንደመሰረተ በመምህራን በኩል ጥራት ያለው ትምህርት ለሕዝብ ልጆች በዕኩልነት እንዲሰጥ ፤የመምህራን የአካዳሚክ ነፃነት እንዲከበርና የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና የመምህራንን የኑሮ ሁኔታ ሊያሻሽል የሚችል የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ በማሳሰብ ከሁሉም በአገሪቱ ከሚገኙ የመምህራን ተወካዮች የተዘጋጁ 20 ጥያቄዎችን በሰኔ 20 ቀን በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት በተደረገው ልዩ የመምህራን ምክር ቤት ስብሰባ የተመረጠ አስተባባሪ ኮሚቴ በሕምሌ ወር 1984ዓም ለሽግግር መንግስት አቀረበ። ለጥያቄዎቹ መልስ በመስጠት ፈንታ ወያኔ ስራዬ ብሎ  በቁርጠኝነት የተንቀሳቀሰው መምህራንን በክልል በመከፋፈሉ ላይ ነበር ። ይህም በኢመማ ላይ ለአራተኛ ጊዜ የመንግስት ጣልቃገብነት ነበር። መምህራን እኛ የምንደራጃው በሙያችን ( በመምህርነት) ነው በማለት የወያኔ  ሴራ በማክሸፍ በሰኔ 20 ቀን 1984ዓም ከተደረገው ልዩ የመምህራን ምክር ቤት ስብሰባ የተመረጠው አስተባባሪ ኮሚቴ የመምህራንን ጉባኤ ለመጥራት ኃላፊነት የነበረው በመሆኑ በሕምሌ ወር 1984ዓም ከሁሉምየአገሪቱ ክፍሎች ተወካይ እንዲልኩ በደብዳቤ ጠየቀ።  ተወካዮችን ለመላክ እምቢ ካለው ከትግራይ ክልል የመምህራን ተውካዮች በስተቀር ከቀሩት የአገሪቱ ክልሎች የመምህራን ተወካዮች በተገኙበት በየካቲት ወር 1985ዓም 14ኛው የኢመማ ጉባኤ ተካሄዶ በዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት የሚመራ አዲስ የኢመማ እመራር መረጠ።ይህ ከሆነ በኋላ ወያኔ  ከፍተኛ ድጋፍ እየሰጠ የጦር ኮር አባላትን ሲቪል ልብስ ለብሰው መምህራን መስለው ተለጣፊ “ኢመማ” በመጋቢት 4 ቀን 1985ዓም መሰረተ።

የተለጣፊው ማህበር መሪ ሆኖ የተመረጠው በኢትዮ_ኤርትራ ጦርነት ወቅት በሻዕቢያ ሰላይነት ከኢትዮጵያ የተበራራው አቶ ዮሐንስ ሀጎስ ነበር። በዚህ ተለጣፊ ማህበር ሕጋዊ የኢመማ አመራር ተከሶ የማህበሩ ባንክ ሂሳብ ውስጥ የነበረው 12 ሚሊዮን ብር ኢመማ እንዳያንቀሳቅስ ተደረገ። ይህም የኢመማን እንቅስቃሴ ለመግታት ሆን ተብሎ የተወሰደ እርምጃ ነው። በ1988ዓም የማህበሩ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት ካንድ የዓለም አቀፍ የትምህርት ባለሙያዎች ድርጅት(Education International = EI) አባል ከሚስተር ቤድያኮ ( የጋና ተወላጅ ከሆኑት) ጋር ከዉጪ አገር ቦሌ ኤይሮፕላን ማራፊያ እንደደረሱ ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትን በመነጠል በመጀመሪያ ማዕከላዊ እስር ቤት አሰሯቸው። በመቀጠልም የሀሰት ክስ ፈብሪካው ከርቼሌ እንድታሰሩ ኣደረገ።በ1985 ዓም በኢመማ ስር የተቋቋመው የአባት/የነባር መምህራን ሊቀመንበር የነበሩት አቶ ከበደ ደስታ (የቀድሞው የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ፕሬዝዳንት)ከዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት ጋር አብረው ማዕከላዊ እስር ቤት እንዲታሰሩ ተድርጎ በእስር ላይ እያሉ በመታማመቻው አስፈላጊውን ሕክምና እንዳያገኙ በወያኔ በኩል ተፅእኖ በመደረጉ በእስር ቤት ውስጥ ህይወታቸው አልፏል፤ በሚያዝያ ወር 1989ዓም የኢመማ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል መምህር አሰፋ ማሩ በጠራራ ጽሐይ ከቤቱ ወጥቶ ወደ ኢመማ ቢሮ ሲሔድ በመንገድ ላይ በወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ተገደለ፤ በ1985 ዓም 42 የዩኒቨርሲቲ መምህራን (በአብዘኛው ባንድ ጎሳ ላይ ያነጣጠረ) ከስራቸው ተወገዱ። በኢመማና በአባላቱ ላይ የወያኔ ጥቃት የከፋ ሆነ፤ በወያኔ ትዕዛዝ በፍርደገምድል ዳኞች ውሳኔ የማህበሩ ጸ/ቤትና ንብረት ( በባንክ የሚገኘን በሚሊዮንየሚቆጠር ብር ለተኤጣፊው እንዲሰጥ ተደረገ)። ተለጣፊው ማህበር የወያኔ ፖለቲካ ክንፍ ሆኖ አገግሎት መስጠቱን ቀጠለ። ኢመማ ግን አሁንም የወያኔ እስረኛ ነው። የሰራተኛው፣ የመምህራን ፣ባጠቃላይ የሙያ ማህበራት ከእስር ይፈቱ።

ማህበሩን ከወያኔ ቁጥጥር ነፃ ለማውጣት የመምህራን ትግል ቀጥሎ የስራ ማቆም አድማዎች በአዲስ አበባ፣ በጎንዳር፣ በወሎ፣ በጎጃም፣ በአርባምንጭ ተካሄደዋል፤ ደመወዝ እንዲጨመር፣ የመኖሪያ ቤት ለመስራት ቦታ እንዲሰጣቸው በተደጋጋሚ ጠይቀዋል፣ በተለያዩ ወቅት ከተለያዩ ት/ቤቶች መምህራን በጋራ በሚያደርጉ ስብሰባዎች፣ በየትምህርት ቤቱ ዓመታዊና ልዩ ልዩ ስብሰባዎችና ኮንፍረንሶች መምህራን የኑሮ ሁኔታቸው ሊሻሻል ባለመቻሉ ለማስተማር የሚያስችግርበት ደረጃ መድረሱን ገልጸው በመንግስት በኩል እርዳታና የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም የሚሰማቸው ጠፍቷል።በዚህም ምክንያት ብዙ መምህራን ከመምህርነት ሙያ ለቀዋል። በቂ ልምድና ስልጠና የሌላቸው የ10ኛ ክፍል ፈተና ያላላፉ ተማሪዎች የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአማራ ክልል እንዲያስተምሩ በማድረግ በትምህርትና በትውልዱ ላይ ግድያ እየተፈጸመ ይገኛል። በቅርቡ ዶ/ር አቢይ አህመድ ከ3ሺ መምህራን ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት ከመምህራን ለቀረበው የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ዶ/ር አቢይ ለመምህራን ደመወዝ ብንጨምር ነጋዴዎች በዕቃዎች ላይ ዋጋ ይጨምራሉ ብለው የመለሱት መልስ በፍጹም ተቀባይነትና አግባቢነት የሌላው መልስ ነው። በሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ጭማሪው ቆሟል ወይ? በምን ምክንያት ነው መምህራን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ሲያነሱ ነጋዴዎች የዋጋ ጭማሪ ያደርጋሉ የሚባለው? በየቀኑ የማስተማር እቅድ አዘጋጅቶ በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉትን የሕዝብ ልጆች በማስተማር ለአገር ዕድገትና ስልጣኔ ወሳኝ ሚና ለሚጨወታው መምህር ኦሮሮ ትኩረት የማይሰጠው?

ለትምህርት ጥራትና ለመምህራን መብት በተደረገው ትግል የእገርንና የህዝብን የመብት ጥያቄዎች በማንሳት በራሳቸው ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ ክቡር ህይወታቸውን የሰጡት እና መምህር የኔ ሰው ገብሬና ጌታቸው እብርሃም ሁልጊዜ የሚታወሱ ናቸው። ሕይወታቸውን ለበጎ ዓላማ ስሉ ሰውተዋል።

በአሁኑ ወቅት አብዘኛው መምህራን የመጨራሻውን የእርከን ጭማሪ ደረጃ ደርሰዋል፤ ምንም የሚጨመር ገንዘብ የለም። ጭማሪው ቆሟል። የሌሎች መስሪያ ቤቶች በአንድ የትምህርት ደረጃና ባንድ ዘመን ተቀጥረው የሚገኙ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪና ዕድገት ባንጻሩ አልቆመም። የኑሮ ውድነት በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው። በዚህ በእቃዎች ላይ በየጊዜው የገበያ ሽያጭ ለውጥ በፍጥነት በሚለዋወጥበት / እየጨመረ በሚሄድበት ሁኔታ መምህራን ራሳቸውን አረጋግተው ትምህርት ለማስተማር በሚችሉበት ደረጃ ላይ አይደሉም። ይህ በጣም አሳሣቢ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ የመምህራንን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻሉ ወሳኝ ነው።

መምህራንን በትምህርት ጥራትና የመብት ጥያቄዎች ላይ በማስተባበር ለድል የሚያበቃው ሙያ ማህበራቸው ኢመማ ነው። ይህ ማህበር ባሁኑ ወቅት መምህሩ ባልወከላቸው የወያኔ ካድሬዎች እጅ ስለሚገኝ ማህበሩን ነፃ ለማድረግ ከትምህርት ቤት መሰረታዊ መምህራን ማህበር ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ድረስ በአዲስ መልክ ለማዋቀር መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆችና ከትምህርት ተጠቃሚ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመተባበር መስራት እንደሚገባቸው በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪ በድጋሚ ያቀርባል።

ድል ለመምህራን ትግል!!
ኢመማ ከወያኔ/ ኢህአዴግ ቁጥጥር ነፃ ይሆናል!!